# የወያኔ የምርጫ ቧልት

**ቢንያም ሳህሉ**

ዲሞክራሲ የሚባለውን ቃል መተንተንና በውስጡ የሚያካትታቸውንና ማሟላት የሚገባውን መስፈርቶች ስናስብ እያንዳንዱ ዕሳቤ ጥልቅ የሆነ ማብራሪያ የሚጠይቅና ለተግባራዊነቱም የሰው ልጅ ከተፈጠረበት ግዜ አንስቶ ባለፈባቸው የህብረተሰብና የታሪክ የእድገት ደረጃዎች እያበለፀጋቸው የመጣ በትግልና በመስዋዕትነት ዕውን የሆነ የህብረተሰብ ግንኙነት ፣ አስተዳደራዊ ፣ አስተዳደራዊ ፣ ማህበራዊ ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ዕምነቶች የነፃነትና ሰው የመሆን ትርጓሜ ዕውን ማድረጊያ ስርአተ ህብረተሰብ ነው ፡፡

የሰው ልጅ በታሪክ ውስጥ በተጓዘባቸው ሂደቶች በጋርዮሽ ስርዓተ ማህበር ውስጥ የመገልገያና የማደኛ መሳሪያዎችን ከድንጋይ ጠርቦ መስራት ከጀመረበት ግዜ አንስቶ በተደረጉ የስራ ክፍፍሎች በጋራ በመኖር ከተሞችን በመገንባት ከአደን ባለፈ በእርሻ ስራም በመሰማራት አስተዳደርን ግድ የሚሉ ሁኔታዎችን ፈጠሩ ፡፡ በነዚህም እድገቶች ሳቢያ በተለያዩ አካባቢዎች የተለያዩ አይነት ስልጣኔዎች ዕድገት ማሳየትና የተሻለ ማህበራዊ ግንኙነቶችን ዕውን አደረገ ፡፡

የሰው ልጅ ስልጣኔ የአባይን ወንዝ ተከትሎ ከተሞችን በመከተም ዛሬ ጥንታዊ ስልጣኔ ብለን የምንጠራቸውን ለዛሬዋ አለማችን ኢኮኖሚያዊ ፖለቲካዊና ማህበራዊ ብሎም ደግሞ ሳይንሳዊ ዕድገቶች ከፍተኛ አስዋፅዖ ያበረከቱ ማኀበረሰቦች ፖለቲካዊ መስተዳደርን ጀመሩ ፡፡ እነዚህም የተመሰረቱ አስተዳደሮች ሰፋፊ ግዛቶችን በመመስረት በንጉሳዊ አገዛዝ ኢኮኖሚያዊ መሰረቶቻቸውን በማጠናከር ለአገዛዛቸው በወቅቱ አመቺ የሆኑ እንደ መንግስት የሚያቆያቸውን ህግጋት በማውጣት የጦት ኃይሎችን በመገንባት የመገበያያ ገንዘብን ወይም ገበያ መወሰኛ ቁሶችን በመወሰን ግዛቶችን በማስፋፋት ትልልቅ ለዕለ ሀያላን ለመሁን በቅተዋል ፡፡

ከነዚህም ጥንታዊ ልዕለ ሀያላን ሙከል ከባቢሎን ፣ ከፋርስና ሜዶን ፣ ከጥንታዊቷ የታላቁ እስክንድር ግሪክ ፣ ከሮማ ፣ ከግብፅ ፈርዖን መንግስት ፣ የቻይና እና የንጉስ ዳዊት ዘመን እስራኤል ብሎም የኢትዮጵያ የአክሱም ስርወ መንግስት ለዓለም ከነ ብዙ ጉድለቶቻቸውም ቢሆኑ ያበረከቱት አስተዋፅዖ በቀላል የሚታይ አይደለም ፡፡ በነዚህ አገሮች ውስጥ በየዘመኑ ታላላቅ ፈላስፋዎች ፣ የስነ-ህዝብ ልሂቃን ፣ የህግ አዋቂዎች ፣ የሂሳብ ሊቆች ፣ የህክምና ጠበብት ፣ የሥነ-ፅሁፍና የቴአትር ፀሀፊ ተውኔቶች ፣ የሙዚቃ ሊቆችና የኢኮኖሚ ጠበብት ፈልቀዋል ፡፡ በዘመናቸውም ዛሬ ዓለማችን ለደረሰችበት የዕድገት ደረጃ መሰረት ጥለዋል ፡፡ አሁን የሰው ልጅ ለደረሰበት ስልጣኔም ሀገራችን ኢትዮጵያ ትልቅ አስተዋፅዖ አበርክታለች ፡፡

ሀገራችን ኢትዮጵያ በአለም ካላት የገዘፈ ታሪክ ባሻገር በሁለቱ ታላላቅ ሀይማኖቶች ያላት ቦታ ትልቅ ከመሆኑም ባሻገር በቁርዓንና በመፅሀፍ ቅዱስ ውስጥም ተደጋግማ የተፃፈች ህዝቧም ተስፋ የተሰጠው መሁኑ በራሱ ለጥንታዊነቷ ትልቅ ምስክር ነው ፡፡ ይህ ክብዙ ሺህ ዓመታት በላይ ያስቆጠረ ታሪክ በህዝቡ መሀል በመከባበር በመቻቻልና በመደጋገፍ ወንድማማችነት ላይ የተመሰረተን አስተሳሰብ በማስረፅ ይህ አስተሳሰብ ህብረተሰባዊ ባህል ሆኖ እስከዛሬ እንዲዘልቅ አስችሎታል ፡፡ ታዲያ ይህ ትስስር በቀላሉ ላይበጠስ አብሮ በመኖር በመጋባት በመዋለድ አንድ ራዕይ ሰንቆ አንድ አገራዊ አስተሳሰብ በመፍጠር ለሀገር የላቀ ፍቅርን መሰረት በማድረግ የነፃነትን ፣ የመስዋዕትነትንና በክብር ኖሮ በክብር ስለ ክብር ስለ ነፃነትና ስለ ሀገር ሰማዕት የመሆንን ጥልቅ አስተሳሰብ እውን ያደረገ የማንነታችን ውጤትና መሰረት ነው ፡፡

ኢትዮጵያ ሀገራችን በፀረ ቅኝ ግዛት እንቅስቃሴ ታሪክ ውስጥ ያላት ስፍራ በቀላሉ የሚታይ አይደለም ፡፡ አድዋ ላይ በአፄ ምኒሊክ ተመርቶ ከመላው ሀገሪቱ ተሰባስቦ በመዝመት ስለ ሀገርና ስለነፃነት የተሰዉት አባቶቻችን በሰማዕትነታቸውና በጅግናቸው በዚያ የጦርነት ውሎ ድል የመቱት ጣሊያንን ብቻ አልነበረም ነገር ግን የቅኝ ገዢዎችን

የበላይነት ያንበረከከ ለፀረ ቅኝ ግዛት ትግልም ፈርን የቀደደ በባርነትና በቅኝ ግዛት ለሚማቅቁ የአለማችን ህዝቦች ተስፋን የፈነጠቀና በትግልና በመስዋዕትነት ነፃነትን መዋጀት እንደሚቻል ያስረገጠ አንፀባራቂ ድል ነበር ፡፡ ይህም ድል ከካሪቢያን ጀምሮ በላቲን አሜሪካ በኢስያና በአፍሪካ የፀረ-ቅኝ ግዛት እንቅስቃሴውን የጫረና የቀጣጠለ ከመሆኑ ባሻገር ለአፍሪካ ደግሞ ሀገራችን ታጋዮችን ከማሰልጠን ገምሮ በነፃነት ትግሉ አስፈላጊውን ድጋፍ ሁሉ በማበርከት የአፍሪካ አህጉር ነፃነትን የተጎናፀፈ ክፍለ ዓለም እንዲሆን አብቅታለች ፡፡

በዚህ ሁሉ የታሪክና የሰው ልጅ የስልጣኔ ዑደት ውስጥ አገራችን በታሪኳ ብዙ ጦርነቶችን አስተናግዳለች ፡፡ በአውሮፓም ሆነ በተቀሩት ዓለማት እንደነበረው የርስ በርስ የስልጣን ሽኩቻዎች በውጭ ሀይሎች ኢትዮጵያን የማዳከምና የመከፋፈል ከተቻለም የማጥፋት እቅድ በተለያዩ ጊዜአት በተለያዩ ሀይሎች የሚረዱ ነገስታት መሳፍንት መኳንንትና ሱልጣኖች ብዙ ደም መፋሰስን ያስከተሉ ውድያዎችን አካሂደዋል ፡፡ ኢትዮጵያችንም ልክ በአለማችን እንዳሉ ዕንደ ማናቸውም ሀገሮች በማህበራዊ ፣ ኢኮኖሚያዊ ፣ መልከዓ ምድራዊና ባህላዊ ትስስሮችና በህያላን መሀከል በሚደረጉ ግጭቶች አልፋ የተፈጠረችና እንደ ጠላቶቿ ሀሳብና እነደ ከሀዲ ቅጥረኛ ጠባብ ልጆቿ ምኞትና ተረት ተረት ባትጠፋም ብዙ ግዛቶቻችንን በግፍ ተነጥቀን ዛሬ የቀረችልን ኢትዮጵያ ልትቀጥል ችላለች ፡፡ የለፉት ገዢዎች በግዛት ዘመናቸው በህዝብ ላይ የተለያዩ ግፎችን ፈፅመዋል ፡፡ የለፉትን ሶስቱን ስርዓቶች እንኳን ብንመለከት በፊውዳላዊቷ ኢትዮያ የመሬት ስሪቱን የሀብት ክፍፍሉንና ሰው በሀገሩ ላይ እንደ ዜጋ ከመከበር ወርዶ ሰው መሆን በራሱ ትልቅ ጥያቄ ውስጥ የገባበት ስርዓት ነበር ፡፡ ያም ስርዓት በህብረተሰብ ሳይንስ ትንተና መሰረት አንድ ነገር የወለዳል ያድጋል ያረጃል ይሞታል ፡፡ ማንኛውም ስርዓትም ጥገናዊ ለውጦችን በማድረግ ከግዜው ጋር ካልተራመደና ጥያቄዎችን መመለስ ካልቻለ በተፈጥሮ ህግ ስለሚገዛ እጣው ከዚያ የዘለለ ባለመሆኑ የንጉሱ አገዛዝ በየካቲቱ ህዝባዊ ዐመፅ ላይመለስ ሊገረሰስ በቅቷል ፡፡

ይህንን ፊውዳላዊ ሥርዓት ከስሩ መንግሎ የጣለው በተማሪዎች የተጀመረው እንቅስቃሴ ግቡን መትቶ ንጉሱን ካስወገደ በኋላ በግዜው በእጃቸው መሳሪያ የነበረ የበታች መኮንኖች በሀይል የነጠቁት የህዝብ የትግል ውጤት የነበረውን ድል የራሳቸውን ፍፁም ጨለምተኛ የነበረና የህዝብን ጥያቄዎች ሁሉ የጨፈለቀ ፈላጭ ቆራጭ ስርዓትን በመመስረት የመሬት ስሪቱን ከፊውዳል የመሬት ከበርቴዎች ወደ መንግስት ይዞታ በማዛወር መሬትን በመጨቆኛ መሳሪያነት መጠቀሚያ አደረገው ፡፡ ይህ አልበቃ ብሎ ቀድሞ እንኳን በከፊል ይታዩ የነበሩ አንዳንድ የመንቀሳቀሻ መንገዶችን ጥርቅም አድርጎ በመዝጋት ጭቆናውን አባባሱት ፡፡ በግዜው በተማሪዎች የተጀመረው የፖለቲካ እንቅስቃሴ ጥያቄውን በማሳደግ ህዝባዊ መንግስት አሁኑኑ የሚል ጥያቄን በማንሳቱ ከግማሽ ሚሊዮን የማያንስ ሀገሬን እና ህዝቤን የለውን አንድ ምርጥ ትውልድ በጠራራ ፀሀይ በቀይ ሽብርና በነፃ እርምጃ በመፍጀት የተረፉትንም በየእስር ቤቱ በማጎር ቀሪዎቹንም አገር ጥለው እንዲሰደዱ አድርጓል ፡፡ በሀገሪቱ ታሪክ ታይቶ በማይታወቅ መልኩ ከፍተኛ ሰቆቃን ማሰቃያ ቦታዎችን በማዘጋጀት በመፈፀም ሰውን መግደልና ማሰቃየት ዕንደ መብት በህግ የታወጀበት ግዜ ነበር ፡፡ ይህ መንግስትም አፈናውንና ጭቆናውን በማባባስ ሀገሪቱን በጦርነት እሳት ይማግዳት ገባ ይህ እድሜውን የማራዘሚያ አንዱ መንገዱ ነበር ፡፡

የኢትዮጵያ ህዝብ በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች ባካሄዳቸው ትግሎች የደርግ መንግስት ስልጣኑን ለወያኔ አስረከቦ ቆራጡና ጀግናው በመባል የሚቆላመጠው መሪ ከውጭ ሀይሎች ጋር በተደረገ ድርድር ወደ ዚምባቡዌ ሲፈረጥጥ አብዛኞቹ ባለስልጣናቱ ደግሞ ዛሬ ዒትዮጵያን እየገዛ ላለው ለወያኔ እጋቸውን ሲሰጡ አንዳንዶቹም በተለያየ ሀዴ ከሀገር ሊፈረጥጡ ሲሉ ተይዘው ዘብጥያ ወርደዋል ፡፡ ይህኛው የስልጣን ሽግግር ኢትዮጵያውያንን ያገለለና በውጭ ሀይሎች የተቀነባበረ ሲሆን የሀገሪቱ ሉዓላዊነትና ግዛታዊ አንድነትን ህዝቡንና ያገባኛል የሚሉ ሀይሎችን ሁሉ ያገለለ የሀገሪቱ ታሪካዊ ጠላቶች ከሁለተኛው የአለም ጦርነት በኋላ በኢትዮጵያና በህዝቧ ላይ በሊግ ዖፍ ኔሽን ከተፈፀመው የበለጠና የከፋ ክህደት የአለም መንግስታትና የተባበሩት መንግስታት ድርጅት የፈፀሙበት ሁኔታ የስከተለ ነበር ፡፡

ይህ ላለፉት 23 ዓመታት ሀገሪቱን እግር ተወርች ጠፍንጎ አላላውስ ያለ የጠባብ ዘረኞች ፋሽስታዊ መንግስት

ሀገሪቱንና ህዝቧን በዘርና በቋንቋ በመከፋፈል ሀገሪቱን ፖለቲካዊ ፣ ማህበራዊ ፣ ኢኮኖሚያዊ ፣ የፀጥታና ወታደራዊ ተቋማት ሙሉ በሙሉ በቁጥጥር ስር በማስገባት ሀገሪቱን ከአንድ ጎሣም ባለፈ ከአድዋ በመጡ የአንድ መንደር ልጆች ቁጥጥር ስር አስገብቷል ። ከሀገሪቱ ጀነራሎች ከ 95% በላይ ኢኮኖሚውን ከ 74% በላይ ከዚሁ ከአንድ መንደር በመጡና የህወሀት አባላት በሆኑ ጥቂት ዘረኛ ሰዎችና ደጋፊዎቻቸው ቁጥጥር ስር የወደቀ ሲሆን ቀሪው 24% በጣም ዝቅተኛ የሆነ የአገልግሎት ሰጪና የግል ግብርና ላይ የተሰማራው ህዝብ ቁጥር የሚካፈለው ነው ። ወያኔ የምርጫ ቦርድ ተብዬውን የሚቆጣጠር ሲሆን ነፃ ጋዜጠኞችንና መብቱን የጠየቀውን ሁሉ በሽብርተኝነት በመክሰስ ብዙዎችን ዘብጥያ አውርዷል ። ፍርድ ቤቶች ነፃ ካለመሆናቸው በላይ ዳኞቹም ሆኑ አቃቢያነ ህጎቹ በወያኔ አባልነታቸው ተመልምለው በሲቪል ሰርቪስ ኮሌጅ የሚመረቁ የወያኔ አላማ አስፈፃሚዎች ስለሆኑ ፍትህ እና የህግ የበላይነት የሚባል ነገር በኢትዮጵያ ውስጥ የማይታሰቡ ነገሮች ናቸው ።

ይህን ሁሉ ያነሳሁበት ምክንያት በመጪው ግንቦት ወያኔ አካሂደዋለሁ ብሎ የሚለፍፍለት የቧልት ምርጫ ምን አይነት ይዘት ይኖረዋል የሚለውን ለመመልከት ነው ። የአፄውን ሥርዓት የፓርላማ ምርጫ ተብዬ ትተን ደርግንና ወያኔን የተመለከትን እንደሆነ ሁለቱን ስርዓቶች በምርጫ ጉዳይ ላይ የሚለያቸው ነገር ቢኖር ደርግ ሁሉን ነገር በአዋጅ የከለከለና ምንም ዓይነት የፖለቲካ ፓርቲንም ሆነ አማራጭ የዜናና የህትመት ውጤቶችን የማይፈቅድ ሲሆን ምርጫውም ቢሆን በእጩነት ከቀረቡ የኢሠፓ አባላት መሀከል ሲሆን ምንም ዓይነት የተለየ አስተሳሰብን ማራመድ ህይወትን የሚጠይቅ ከመሆኑም ባሻገር ህዝቡም ቢሆን ራሽን እንዳይከለከልና አንዳንድ አገልግሎቶችን ከቀበሌ በጠየቀ ግዜ እንዳያጣ ሳይወድ በግድ ምርጫውን የሚሳተፍበት ሁኔታ ነው የነበረው ።

ወያኔ ለስሙ ዲሞክራሲን አራምዳለሁ ፣ ፌደራላዊ ሥርዓትን መስርቻለሁ ፣ የብሄር ብሄረሰቦች መብትተከብሯል ፣ የፕሬስ ነጻነትም ተረጋድጧል በማለት በሞኖፖል በሚቆጣጠራቸው የዜና አውታሮቹ አታካችና አሰልቺ ፕሮፖጋንዳውን ይነዛል ። ወየኔ ስልጣን በያዘባቸው በመጀመሪያዎቹ አመታት የፕሬስና ለአፈናው እንዲመቸው ሁሉም የተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎች አባላቶቻቸውን የማሳወቅ ግዴታን ለመስረግና አስፈራርቶ ለመግዛት እንዲመቸው ቢደነግግም በአንፃራዊነት የተሻለ የሚባል የመንቀሳቀሻ ክፍተቶች ነበሩ ። ከመነሻው ጀምሮ የምርጫ ማጭበርበሩ ቢኖርም በ 1997 ቱ ምርጫ ወያኔ በደረሰበት ሽንፈትና የፖለቲካ ኪሳራ ሳቢያ ብዙ ሰዎችን አግዞ በየጦር ካንፑ በማሰር ከሁለት መቶ በላይም በመግደል ህዝቡ ታግሎ የገኘውን ድል በጠመንጃ ሀይል ከነጠቀ በኋላ ቀድሞ የሰረጋቸውን የፖለቲካ ድርጅቶች በመበታተን መሪዎቻቸውንም በማሰርየሚበዙትንም በማሳደድ ለይስሙላ እንኳን የነበረውን የመጫወቻ ሜዳ የለ ምንም ይሉኝታ በመዝጋት ስልጣኑን ሙሉ በሙሉ ተቆጣጥሮታል ። ታድያ ወያኔ ጭንብሉን አውጥቶ ከጣለ ከአስር ዓመታት በኋላም ነፃና ፍትሀዊ ምርጫ አካሂዳለሁ በማለት ሲራወጥ ይታያል ።

በሀገራችን በኢትዮጵያ ውስጥ ምንም ዓይነት ነፃ ፕሬስ በሌለበት ፣ የሀገሪቱን ጦር ሙሉ በሙሉ ወያኔ በሚቆጣጠርበት ፣ ፍርድ ቤቶችና ፖሊስ የመጨቆኛና የአፈና መሳሪያዎች በሆኑበት ፣ ምርጫ ቦርድ ተብዬው በማያገባው ገብቶ የፖለቲካ ድርጅቶችን በሚያፈርስበትና የወያኔ ሌላኛው የመጨቆኛ መሳሪያ በሆነበት ፣ ከሃምሳ ሺህ በላይ የፖለቲካ እስረኞች በየማጎሪያና ማሰቃያ እስር ቤቶች ብሎም ከምድር በታች ባሉና ባዶ 6 በመባል በሚታወቁ የጨለማ እስር ቤቶች ስየልን እየተቀበሉ ባሉበት ፣ ጋዜጠኞች ህዝብ የማወቅ መብት አለው በማለታቸው እውነትን በመዘገባቸውና በመፃፋቸው በሽብርተኝነት ተከሰው ወህኒ በተወረወሩበት ፣ የህዝብ ልጆች የሆኑን እነ ፀጋዬ ደብተራውን በጦር ምረኮኝነት ከያዘ በኋላ የለምንም ፍርድ በወያኔ ትዕዛዝ በሚረሸኑበት ፣ የዘር ማጥፋትና የዘር ማጽዳት ዘመቻ በተለያዩ የሀገሪቱ ክልሎች በሰፊው በሚፈጸምበት ሁኔታ የሚካሄድ ምርጫ ምን ዓይነት ምርጫ ነው የሚሆነው? ዶሮን ሲያታልሏት እንዲሉ አበው ወያኔ ውሸቱ ሁሉ አልቆበት ወዳጆቹ ሁሉ አላምን ያሉበትና አንዳንዶቹም ዕንኳን የሚያቀርቡለትን እርዳት እስከማገድ የደረሱበት ሁኔታ ላይ እንገኛለን ። ይህ የወያኔ የቧልት ምርጫ ለኢትዮጵያውያን ሌላ የመከራ ዘመን ማራዘሚያ ስለሆነ ሁሉም

ህዝብ የምርጫው የመጫወቻ ህግ እስካልተቀየረና ምርጫ ቦርድና ፍርድ ቤቶች ነፃ ችስካልሆኑ ድረስ ፣ የፖለቲካ እስረኞች ጋዜጠኞችንና የሰብዓዊ መብት ታጋዮችን ጨምሮ የለምንም ቅድመ ሁኔታ እስካልተፈቱና የታገዱ የፖለቲካ ድርጅቶችም ሆኑ የሲቪክክና የሙያ ማህበራት በነጻነት የመንቀሳቀስ መብታቸው እስካልተጠበቀ ድረስ ፣ ፍትህዊ የሆነ የዜና ማሰራጫዎች የአየር ሽፋን እስካልተፈቀደና የማፈኛ መሳሪያ የሆነው የሽብርተኛ ህግና ህገ መንግስት ተብዬው ህገ ወያኔ ማሻሻያ እስካልተደረገበት ድረስ ህዝቡ ይህንን ምርጫ በተደራጀና በተቀነባበረ መልኩ ቦይ ኮት ማድረግ አማራጭ የሌለው ምርጫ ሊሆን ይገባል ፡፡ እስከዚያው ግን በጥብቅ እና ህቡዕ በሆነ የአደረጃጀት ዘዴ ህዝቡ በሙያና ሲቪክ ማህበራት ፣ በጎበዝ አለቃ ፣ በፖለቲካ ድርጅቶችና በተለያዩ ማህበራዊ ተቋማት በመደራጀት የሀገራችን ጠላት የሆነውን ይህንን ሰው በላና አንባገነን ስርዓት ገርስሰን በምትኩም ህዝብ የስልጣን ምንጭ የሚሆንበትንና የህግ የበላይነት የሚሰፍንበትን ዲሞክራሲያዊ ሰርዓት በህብረት ቆርጠን እንነሳ ፡፡

እናቸንፋለን!

ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር!

ቢንያም ሳህሉ